**የዞራስተር ፍካሬ: ወደ ሁሉምና ወደ ማንም** በፍሬድሪች ዊልሄልም ኒሺ የተደረሰ የፍልስፍና ልቦለድ* ነው። መጽሐፉ በ1883 እና 1885 (እ.ኤ.አ) መካከል በ4 ክፍል የተደረሰ ሲሆን በጊዜው ይሰራበት ከነበረው የአስተሳሰብ ዘዴ ለየት ባለ መልኩ የፍልስፍናን እና የግብረገብን ጥናቶች መርምሯል። የመጽሃፉ አትኩሮቶች፦ የዘላለማዊ ምልልስ፣ ኃይልን መፍቀድ (*ፈቃድ እዚህ ላይ ጠንካራ ፍላጎት ማለት ነው)፣ የአምላክ በጊዜው በነበሩ አውሮጳውያን ልብ ውስጥ መሞት፣ ስለዚህም የአዳዲስ ዋጋ ወይም ህግጋት አስፈላጊነት፣የበላይ ሰው (*በኒሺ አስተሳሰብ የሰው ልጅ በጦጣዎችና በበላይ ሰው መካከል ያለ ፍጡር ነው) መምጣት ትምህርቶች ነበሩ። [1] ጽሁፉ የመጽሐፍ ቅዱስ አጻጻፍ ስልት ይከተል እንጂ የውስጡ ፍሬ ነገር ግን የክርስትናና አይሁድ ሃይማኖቶችን መሰረታዊ እምነቶች የሚጻረር ነበር። ኒሺ ይህን መጽሐፍ " ከሰዎችና ከጊዜ 6000 ጫማ" እርቆ እንደጻፈ ይናገራል፣ ማለቱም የመጽሃፉን ሃሳቦች በተራራ ላይ እያለ እንዳገኛቸው ለማስገንዘብ ነበር።[2]

ኒሺ "የዞራስተር ፍካሬ" ብሎ የሰየመውን መጽሃፍ "ስርዓት አልባ"(ጥራዝ ነጠቅ) በሆነ ዘዴ ስለጻፈው ለተመራማሪወች እጅግ አስቸጋሪ ሆነ። ይሁንና ተመራማሪወች አንድ አንድ ቋሚ የሆኑ የመጽሃፉን ይዘቶች ማስተዋላቸው አልቀረም፦

- የበላይ ሰው፡ ለኒሺ የበላይ ሰው ማለት በራሱ ላይ ሙሉ ቁጥጥር ያለው ግለሰብ፣ እምቅ ኃይሉን ወደ ስራ የተርጎመ ሰው ማለት ነው። አሁን ያለው የሰው ልጅ (በኒሺ አሰተያየት) በእንስሳ እና በዚህ በበላይ ሰው መካከል ያለ ፍጡር ነው።

- የዘላለም ምልልስ፡ ማናቸውም የተከሰቱ ነገሮች እንደገና ይከሰታሉ፣ አሁን የሚከሰቱ ነገሮች ድሮም ተከስተው ነበር ለወደፊቱም እልፍ አዕላፍ ጊዜ ይከሰታሉ! ይህ አለም ልክ እንደምናየው ሆኖ እንደገና ይከሰታል፣ ሰውም ይሞታል ግን ልክ በነበረበት መልኩ በነበረበት አለም ተመልሶ ይመጣል።

- ኅይል መፍቀድ፡ የሰው ተፈጥሮ መሰረታዊ ባህርይ ነው። ማናቸውም የምንሰራቸው ነገሮች፣ እንደ ኒሺ አስተያየት፣ የዚህ መሪ ሃሳብ መገለጫ ናቸው። ከመራባት፣ ደስታ፣ ሐሴት ጋር ሲነጻጸር የበለጠ መሰረታዊ ሲሆን የኅይል መፍቀድ ሁሉም ህይወት ያለው ነገር ሁሉ ከከባቢው አለም ጋር የሚያደርገውን ትግል ጠቅልሎ የሚይዝ ጽንሰ ሃሳብ ነው።

- በኃጥያትና ጽድቅ ስራወች በተሰኙ ተቃራኒ የክርስትና ሃሳቦች ላይ ብዙ ትችት መመስረት። በኒሺ አስተያየት እኒህ ነገሮች የሰው ልጅ ፈጠራወች እንጂ በተፈጥሮ የሚገኙ አይደሉም። በሱ አስተያየት የሰው ልጅ ተግባር መለካት ያለበት አስቀድሞ በተቀመጡ የግብረ ገብ ዋጋወች/ህጎች (ጥሩና መጥፎ) ሳይሆን የተግባሩን መዘዝ በመለካት ነው።

## ማውጫ


- 1 መጽሐፉ ባጭሩ
    - 1.1 ክፍል ፩
    - 1.2 ክፍል ፪
    - 1.3 ክፍል ፫
    - 1.4 ክፍል ፬

- 2 ከፍካሬ ዞራስተር የተወሰዱ ጥቅሶች
- 3 ማጣቀሻ


# መጽሐፉ ባጭሩ

በመጽሃፉ መግቢያ ላይ ዞራስተር 30 አመት ሲሞላው ወደ ተራራ እንደወጣና በዚያ ከሰወች ተለይቶ ብዙ ጥበቦችን እንደሰበሰብ እናነባለን። 40 አመት ሲሞላው ያከማቸውን ጥበብ ለማካፈል ከተራራው ወረደ። የመውረዱ ዋና አላማ "የበላይ ሰው"ን መምጣት ለመስበክ ነበር። የበላይ ሰው፣ በዞራስተር አስተሳሰብ፣ ከሰው በላይ የሆነ ፍጡር ማለት ነው፡ ልክ የሰው ልጅ ከጦጣወች በላይ የሆነ ፍጡር እንደሆነ።

በዞራስተር ግምት ዘመናዊው ሰው የወኔ ግሸበት፣ ባዶነትና አጠቃላይ የህይወት ውዥንብር ስለገጠመው አዲስ ትምህርት ያስፈልገዋል። በዞራስተር አስተሳሰብ የዘመናዊው ሰው መንፈሳዊ ግሸበት ምክንያት የአምላክ መሞት ነው። በርግጥ አምላክ ለመሞት አይቻለውም ሆኖም ግን በዞራስቶር አስተሳሰብ አምላክ ሞተ ማለቱ ዘመናዊው ሰው በአምላክ ላይ ያለው እምነቱ ሞተ ማለት ነው። ስለሆነም የድሮወቹ ሰወች ብዙ አስደናቂ ስራወችን ለአምላክ ሲሉ ቢሰሩም የዘመናዊው ሰው ግን ይህን እመንቱን በማጣቱ አጠቃላይ ዘመናዊ ህብረተሰብ መሪ ሃሳብ የማጣት፣ የመበስበስና ተስፋ የማጣት ምልክቶች አሳየ። ህግን የሚሰጥ በሰው አምሳያ ያለ አምላክ ለአዲሱ ሳይንሳዊና ዘምናዊ ህብረተሰብ እጅግ ኋላ ቀር መስሎ ታየ። ስለሆነም በተለይ በተማሩ ሰወች ዘንድ የአለም የህይወት ትርጉምና የግብረገብ ስርዓት እጅግ ዝብርቅርቅ ያለ ሆነ። ዘመናዊ ሰው ባዶነት "ኒሂልዝም"( የህይወት ትርጉም ማጣት) የሚባል ችግር ተጋረጠው፣ "የዞራስተር ፍካሬ" ዋና አላማ ይህን ባዶነት መታገል ነበር። በኒሺ አስተሳሰብ አዲሱ የ"በላይ ሰው" ትምህርት ለዚህ ዘመናዊ ኒሂሊዝም (ባዶነት) ፍቱን መድሃኒት መሆን ነበር።

ዞራስተር ከተራራው ወርዶ በሰወች መካከል እንዲህ ሲል ሰበከ: *የሰው ልጅ በአሁኑ ሰዓት ያለበትን መናኛነት (ተራነት)ና የከሰረ ስልጣኔ በማሸነፍ የ"በላይ ሰው"ን መፍጠር አለበት፡ «የሰው ልጅ ሊሸነፍ የሚገባ ነው። ለማሸነፍ እያንዳንዳችሁ ምን አድርጋችኋል?»* ሆኖም ግን ይህ ሰበካው ተቀባይነት አጣ። ህዝቡም መልሶ «የበላይ ሰውህን እዚያው ለራስህ» ብለውም ተሳለቁበት። የተመቻቸና ጥሩ ኑሮ ከመፈለግ ውጭ የበላይ ሰውን እንደማይፈልጉ ነገሩት። ህይወት የበለጠ ትርጉም ካልተሰጠው በርግጥም ከደስታ ውጭ ምንስ ያስፈልጋል? በዚህ ምክንያት የስልጣኔ ዋና ዓላማ ተራ መናኛ ሆነ፣ እርሱም፡- "ከፍተኛ ደስታ ለከፍተኛ ቁጥር ላለው ሰው" ሆነ።

ይህ ተራነት ዞራስተር ለህዝቡ ያለው ጥላቻና ንቀት እንዲያድግ አደረገ ( ምንም እንኳ ከጊዜ ወደጊዜ ሊያዝንላቸውና ሊረዳቸው ህሊናው ቢግደረደርም)። ተማሪውም ሆነ ያልተማረው፣ ፖለቲከኛውም ሆነ ፈላስፋው፣ ሰዓሊውም ሆነ ፕሮፌሰሩ፣ ሁሉም የተደላደለ ህይወት ከመሻት ውጭ ውስጣቸው ያለውን እምቅ ስብዕና ለማሳደግ የማይጥሩ ሆኖ አገኛቸው። ካደረበት ንቀት የተነሳ ዞራስተር ብዙ ተከታይ ከማፍራት ይልቅ ሊግባባቸው የሚችሉ ጥቂት ፈርጥ የሆኑ ሰወችን ፍለጋ ጀመረ፡ ተራ(መናኛ) ነገሮችን ከህይወት ለማግኘት የሚሞክሩን ሳይሆን፣ ከፍተኛ ነገርን ለማግኘት የሚሞክሩትን። ፍለጋው ጥቂት ሰወችን ስላስገኘለት ለኒህ ለተመረጡት "ማስተማር" በጥብቅ ጀመረ።

የመጨረሻው የመጽሃፉ እትም 4 ክፍሎች አሉት። እያንዳንዱ ክፍል ለማብራራት ብዙ ቦታ ስለሚይዝ ከዚህ በታች በየራሳቸው ገጽ ማብራሪያቸው ሰፍሯል። ይመልከቱ።

## ክፍል ፩

*ዋና መጣጥፍ፡- የዞራስተር ፍካሬ ክፍል ፩*

**ክፍል ፪**

*ዋና መጣጥፍ፦ [የዞራስተር ፍካሬ ክፍል ፪]*

**ክፍል ፫**

*ዋና መጣጥፍ፦ [የዞራስተር ፍካሬ ክፍል ፫]*

**ክፍል ፬**

*ዋና መጣጥፍ፦ [የዞራስተር ፍካሬ ክፍል ፬]*

# ከፍካሬ ዞራስተር የተወሰዱ ጥቅሶች

- ህይወትን የምናፈቅር መኖር ስለምናወቅ ሳይሆን ማፍቀር ስለምናውቅ ነው።
- በፍቅር ውስጥ ሁል ጊዜ ዕብደት አለ። በዕብደት ውስጥ ደግሞ ሁልጊዜ ምክንያት አለ።
- አንቺ ታላቅ ኮከብ! ፍንትው ብለሽ የምታበሪላቸው ባይኖሩ ደስታሽ ምኑ ላይ ነበር?
- መብረርን የሚማር መጀመሪያ መቆምን፣ ከዚያም መራመድን፣ ብሎም መሮጥንና ዛፍ መውጣትን እንዲሁም መደነስን መማር አለበት፣ ወደ መብረር መብረር አይቻልም!
- እውነትን መናገር - በጣም ጥቂት ሰወች ይችላሉ! ከነዚህ ከሚችሉት ግን የሚፈፅሙት የሉም`!
- ደፋርነት፣ ደንታ ቢስነት፣ አላጋጭነት፣ ጸበኛነት-- ጥበብ ከኛ እኒህን ትፈልጋለች፡ ሴት ናትና የምትወደውም ጦረኛን ብቻ ነው።
- እራሱን የማያዝ መታዘዝ አለበት። ብዙወች እራሳቸውን ማዘዝ ይችላሉ፣ ነገር ግን ለራሳቸው ከመታዘዛቸው በፊት ብዙ ይጎላቸዋል!
- ህብረተሰብ ተኩላውን አላምዶ ውሻ አደረገ። የሰው ልጅ ከሁሉም የሚበልጥ ለማዳ እንስሳ ነው!
- አንድ ልምድ አጀማመሩ በሩቅ የዘመን ጭጋግ እየተሸፈነ ከሄደ፣ አመሰራረቱም እየተምታታ ከመጣ -- በክብር እያደገ ይሄዳል። ከትውልድ ወደ ትውልድም ክብሩ እየጨመረ ይሄዳል። በመጨረሻ ልምዱ ቅዱስ ይሆንና በሰወች ዘንድ ድንቅ ይሆናል።
- ሰው በንዴት አይገድልም፣ በሳቅ እንጂ።
- በቁመና ለማደግ፣ ወደብርሃንም ለመጠጋት በተፈለገ ጊዜ፣ ስርን ወደ መሬት መላክ ያስፈልጋል፣ ወደ ድቅድቅ ጨለማው፣ ወደ ጥልቁ - ወደ መጥፎው።
- እውነተኛ ወንድ ሁለት ነገር ይፈልጋል፦ አደጋና ጨዋታ። ለዚያ ሲልም ሴትን ይፈልጋል፣ ከሁሉ በላይ አደገኛ የሆነች መጫወቻ።

- "የታላላቆቹ ተራሮች አመጣት ከየት ይሆን?" ብየ ጠይኩ። ከባህር እንደመጡ ደረስኩበት፣ ማስረጃውም በአለቶቻቸውና በከፍተኛ ገጽታቸው ተጽፎ ይገኛል። ታላላቅ ከፍታወች የሚመጡት ከታላላቅ ጥልቀቶች ነው።

- **ነጻ ከምን?** ለዞራስተር ደንታ ይሰጠው ይመስል! ይልቁኑ ብሩህ አይኖችህ እንዲህ ይበሉ፡ **ነጻ ምን ለማድረግ?**

- ሳንደንስበት ያለፈን ቀን እንደጠፋ ቀን መቁጥር ይገባል። እንዲሁ በሳቅ ያልታጀበን እውነት ውሸት ማለት ይገባል።

- መተኛት ቀላል ጥበብ አይደለም፡ ለዚህ ተግባር ሲባል ቀኑን ሙሉ መንቃት ግድ ይላል።

በዚህ የመጽሃፉ ክፍል የዞራስተር ዋና ነጥቦች በስድስት ዋና ዋና ሃሳቦች ይጠቃላል።

- የመጀመሪያው የዞራስተር ነጥብ አጠቃላይ ሜታፊዝክን መካድ ነው። ሜታፊዚክ ማለት በተጨባጩ አለም ጀርባ የማናየው፣ የማንዳሰሰው፣ የማናሸተው እውነተኛ አለም አለ በማለት ይህን አለም ለማግኘት የሚጥር የፍልስፍና ዘርፍ ነው። በዞራስተር አስተያየት አንድ አለም ብቻ አለ፡ እርሱም ተጨባጩ አለም ነው።

- ሁለተኛው የዞራስተር ነጥብ የአይምሮና አካል ክፍፍልን መካድ ነበረ። በተለምዶ ሰው አካል አለው ብንልም በዞራስተር አስተያየት ሰው እራሱ አካል ነው። የሰው ልጅ ከማይጨበጥ ምናባዊ ነገር (አዕምሮ) እና ከተጨባጭ ነገር (አካል) የተሰራ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ከአካል የተሰራ ነው። በነደካርት የተነሳው ቀልበኛ ፍልስፍና የሰውን ልጅ ከሁለት (አዕምሮና ሰወነት) ከከፈለ ወዲህ የሰው ልጅ የስራ ውጤቶች ብዙ አመርቂ አልሆኑ፣ ይልቁኑ የጥንቶቹ ከያኒያን በ"ደማቸው የጻፉዋቸው መጽሃፎች" (በአይምሮ ከተጻፉ ዘመናዊ መጽሃፎች) በተለየ መልኩ ስሜት የሚነኩ እንደነበሩ አስተማረ። የሰው ልጅ "አዕምሮ" ከሆነ ወዲህ ስራው ሁሉ በቀመር የተወጠረና ምንም ስሜት የማይቀስቀስ ሆነ።

- ዞራስተር ሙሉ በሙሉ የግለሰብ ነጻነትን ይደግፋል። ግብረገብ፣ የጋራ ሰላምና፣ ይሉኝታ ለዞራስተር ደንታው አይደሉም። የህይወት ኃይሎች በምንም አይነት መታፈን የለባቸውም። የተመረጡ ነፍሶች የመንጋወችን ግብረ ገብና ስርዓቶች ወደጎን ትተው የራሳቸውን ዋጋ/ህግ አውጥተው የራሳቸውን አላማ ለማስፈጸም ይታገላሉ። ትክክለኛው የህይወት ጣዕም በህግጋትና ግብረገብ የተጋረደ ሳይሆን ከኃጢያትና ጽድቅ ወዲያ ርቆ የሚገኝ ነው።

- ሙሉው የግለሰብ ነጻነት "ሁሉ በሁሉ ላይ" ጦር እንዲያነሳ ሊያደርግ ይችላል። ይህ ግን በዞራስተር አይን ምንም አይደለም ምክንያቱም ሁሉም ህይወት ያለው ነገር "ኃይልን ይፈቅዳል"፡ ሁሉም ህይወት ያለው ነገር እራሱን ያረጋግጣል፣ ለመኖሩም ምልክት ትግል ያካሂዳል። ሄራክሊተስ እንደጻፈ "ጦርነት የሁሉ ነገር አባት ነው"፣ በዞራስቱራ አስተያየት ያለፍልሚያ ምንም ጥቅም ያለው ነገር አይመጣም። ዞራስተር ለጓደኞቹ የሚመክረውም "በአደጋ ኑር!" እያለ ነበር። ፍቅረኛሞች እንኳ ሳይቀሩ ችግር ሊገጥም እንዲችል መረዳት አለባቸው፣ በፍቅር መጎዳት የሚፈራ ወይም ቂም የሚያሲይዝ ሳይሆን እራስን ለማሳደግና አዳዲስ ነገሮችን ለመረዳት የሚያገለግል ዕድል ነው። ጦርነት ተቀባይነት ያለው መሳሪያ ብቻ ሳይሆን ተቀባይነት ያለው ግብም ነው።

- እራስን መወሰን ለዞራስተር ፍልስፍና ዋና ቁልፍ ነው። ይህ አለም ከላይም ሆነ ከታች ከጎንም ሳይቀር የተሰጠው ትርጉምም ሆነ ህግጋት የሉትም። ሁሉም ሰው የራሱን ትርጉምና ህግጋት በመፍጠር እራሱን ይወስናል። ሁሉም ሰው ልክ እንደሙሴ የራሱን ጽላት እንዲቀርጽ እንጂ ለሁሉም የሚሰራ ከላይ የተላለፈ ህግ የለም። ከዚህ አንጻር እራስን መወሰን ባንድ በተስተካከል የአለም ስርዓት ውስጥ ራስን መቻል ሳይሆን ከትርምስ ውስጥ የራስን አለምን እንደመፍጠር ነው።

- ህይወት ሂደት እንጂ ሁኔታ አይደለም። አንድ የሰው ልጅ በሂደት ላይ ያለ እንጂ፣ ቆሞ ያለ የሆነ ነገር አይደለም። እራስን እንደ አንድ ቋሚ ነገር ማሰብ በዞራስተር ስህተት ነው። በመጠበቅ፣ እውቀትንና ሃብትን ዝም ብሎ በማከማቸት ህይወት አይኖርም፣ ይልቁኑ እራስን በየጊዜው በማሸነፍና እራስን በመቀየር ህይወት ይኖራል።

## *ሶስቱ ሽግግሮች*

- ሌላው የዚህ ክፍል ዋና ሃሳብ ሶስቱ ሽግግሮች ናቸው።የሰው መንፈስ እውነቱንና እራሱን ለማወቅ 3 ከባድ ለውጦች እንደሚያካሂድ ዞራስትራ በዚህ ክፍል ሲያስረዳ፦

  " እነሆ ነፍሳችሁ ሶስት ጊዜ ይሻገራል፡ እንኪያስ ግመል ነበራችሁ፣ ግመሉ አምበሳ፣ በመጨረሻ አምበሳው ህጻን ልጅ!"

ትርጉሙም የመጀመሪያው የመንፈስ ለውጥ ወደ ግመል ሲሆን ይህም "ትሁት መንፈስ"ን ያመላክታል፡ እራስን መካድ፣ በሃብት መቆጠብን፣ መታዘዝንና ችግርን መቋቋምን። ይህም ግመልን እራሷን ዝቅ አድርጋ የጭነት እንስሳ እንደሚያደርጋት ባህርይ ነው።

> " **መ**ጫን ያለበት መንፈስ እንዲህ ይጠይቃል "ከሁሉ ነገር ከባዱ ምንድን ነው?" መልሶም "በጫንቃየ ላይ ጭነቴን አዝየ በጥንካሬየ ሐሴት ማድረግ አይደለምን? እራሴን በማዋረድ ኩራቴን መግደል አይደለምን? የዋህነቴን በማጋነን ጥበቤን መፎተት አይደለምን?"

ከዚህ የግመል አለም ወደ አንበሳነት የሰው መንፈስ ለሁለተኛ ጊዜ ይሻገራል። በዚህ ጊዜ ከጭነት ነጻ ይሆናል፣ ከላይ ወደታች በተዘርጋ የሃይል አሰላለፍ ቁንጮውን ለመያዝ ጥረት ያደርጋል፣ ራስ ገዝ ሆኖ ነጻነቱን በራስ ገዝነትና በሃያልነት ይደነግጋል። በታላቁ ዘንዶ ላይ ጦርነት ይክፈታል፣ የቀድሞውን ግብረገብ ጽንሰ ሃሳብ አውልቆ ይጥላል።

> "ለራሱ ነጻነትን ለመቀዳጀት፣ በህግጋት ላይ ሳይቀር "እምቢ" ለማለት፣ ወንድሞች፣ ለዚያ ለዚያ አንበሳ ያስፈልጋል። አዳዲስ ህግጋትን የመፍጠር መብት እንዳለ ለማወቅ ለተሸካሚና ለአክባሪ ነፍሳት እጅግ አስቸጋሪ ነው። ይህ ተግባር ለነዚህ እንደ ማደን እና የሚታደን እንስሳ ስራ ነው።"

አንበሳ እንግዲህ የነበረውን እምቢ በማለት የሚያፈርስ እንጂ አዲስ የሚፈጥር አይደለም። ስለሆነም የሰው መንፈስ አዳዲስ ህግጋትን ለመፍጠር ለ3ኛ ጊዜ መሻገር ይኖርበታል። በዚህ የመጨረሻው ሽግግር መንፈሱ ከአንበሳ ወደ ህጻን ይቀራል። ህጻኑ አዲስ ጅማሬን፣ ንጹህ የዋህነትን የሚወክልና የድሮወቹን ህግጋት ድል ካደረገ በኋላ አዲስ ዋጋወችን ፈጣሪ ይሆናል።

> "ሕጻን የዋህነት ነው፣ ያለፈውን መርሳትም ነው፣ አዲስ ጅማሬ፣ ጨዋታ፣ እራሱን የሚያሽከረክር ጎማ፣ የመጀመሪያ እንቅስቃሴ፣ ቅዱስ የሆነ "አው-ማለት"። አወ! ወንድሞች፣ የፈጠራ ጨዋታ ቅዱስ የሆነ "አወ"

ማለትን ይጠይቃል፡ መንፈስ የራሱን ፈቃድ ይፈቅዳል፣ አለሙን ያጣ እንግዲህ *የራሱን* አለም ያገኛል።"

ሁሉ ነገር በህጻን ልጅ ተጀምሮ እንደገና በህጻን ማብቃቱ የኒሺን የዘላለም ምልልስ ጽንሰ ሃሳብ የሚያንጸባርቅ ነው። በዚህ የዘላለም ድግግሞሽ የሰው ልጅ እራሱን በማሸነፍ ከነበሩበት ድክመቶች ሁሉ ነጻ በመውጣት አዲስ አይነት ሰው – የራሱ ህግ/ዋጋ ያለው የበላይ ሰው ይፈጥራል።

እኒህን ነጥቦች ለተመረጡ ተከታዮቹ ካስተማረ በኋላ ዘራስተር ወደተራራ ዋሻው እንደተመለሰ መጽሃፉ ያትታል። የዚህ ምክንያቱ ያለሱ ተጽዕኖ ተከታዮቹ በራሳቸው ውሳኔ የራሳቸውን ሃሳብ እንዲያዳብሩ ነው። አስተማሪነቱን ማቆሙም ይህን የፍልስፍናውን ግብ ላለማጣረስ ነበር።

> "ዘሩን እንደዘራ ገበሬ ማደጉንም እንደሚጠባበቅ፣ ዘራስተር ከሰወች በማምለጥ ወደአምባው፣ ወደ የብቸኝነት ዋሻው ተመለሰ"

ዘራስተር በዚህ ወቅት ከተራራው ወርዶ ስላጋጠመው ሁኔታ ማንሰላሰል ጀመረ፣ በተለይ "ኃይልን መፈለግ" ("ኃይልን መፍቀድ") የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ ተገነዘበ። በዞራስተር አስተያየት ኃይልን መፍቀድ ህይወት ያለው ነገርን ሁሉ የሚገፋፋ መሰረታዊ ጉልበት ነው። ይህ ሃይል፣ በዞራስተር አስተያየት፣ ለመኖር ከመፍቀድ ሁሉ በላይ የሆነ ኃይል ነው። ኃይልን መፍቀድ በብዙ መንገድ ይገለጻል፣ ለምሳሌ፦ ባህታዊወች በመብላት ፍላጎታቸው ላይ ያላቸው ሃይል፣ ግለሰቦች በህብረተሰብ ውስጥ የሚያሳዩት የእራስን ስልጣን የማረጋጥ ሁኔታ፣ አንድ የኪነ ጥበብ ሰው በስራው ላይ የሚያሳየው ሙሉ ክህሎት፣ ወዘተ..።

> በሄድኩበት ቦታ ሁሉ ያገኘሁት ህይወት ያለው ነገር ሁሉ ኃይልን ይፈቅዳል፣ የሚታዘዙት እንኳ ሳይቀር ጌታ ለመሆን ይፈቅዳሉ! ደካሞች ለጠንካሮች ለመታዘዝ በሌላ ሳይሆን በራሳቸው ፈቃድ ይስማማሉ፣ ደካሞቹ ደግሞ በተራቸው ከነሱ የበለጠ ደካማ ለሆነው ጌትነት ይፈቅዳሉ፡ ይህ ጨርሰው ሊተውት የማይፈቅዱት ደስታቸው ነው!
> ታናናሾቹ ከነሱ ያነሱት ላይ ኀይል እንዲኖራቸው ለበላዮቻቸው ፈቀቅ እንደሚሉ ሁሉ ከሁሉ የበላይ የሆነው ለአደጋና ከባድ ፈተና እንዲሁ ፈቀቅ ይላል፣ ለኀይል ሲልም ህይወቱን አደጋ ላይ ይጥላል። የሁሉ ታላቅ ፈቀቅ ማለት ለህይወት አስጊ ለሆነ አደጋና በሞትና በህይወት ቁማር ለመጫወት ነው።

በዚህ ክፍል ግማሽ አካባቢ ዞራስተር ብዙ ስራው የጭንቅላት ስራ እንደሆነ ተረዳ፣ ስለዚም ቶሎ ብሎ መዝፍንና መደነስ ተያያዘ። ደመነፍስ ኪነጥበብ የሆኑት ዘፈንና ዳንስ፣ የሰው ልጅ ኀልውና ዋና አካል መሆንቸውን በማስረገጥ ብዙ የጥበብና የብርሃን ተሸካሚ መሆን ጥሩ እንዳይደል አስረዳ። ይህ ሁኔታ ስለአጠቃላይ የህይወት ትርጉም ያለውን አስተያያእት ተፈታተነው፡ በፍልስፍናና በትምህርት የህይወት ትርጉም ራዕይ እንደማይገለጥለት ተረዳ። አስተማሪና አዋቂ ብቻ ከመሆን ይልቅ እንደ ዘፈንና ጭፈራ ያሉትን የህይወትን ደመነፍሳዊ ክፍሎች በመቋደስ የህይወት እውነታወች መረዳት እንዲቻል ተገነዘበ።

ከዘፈንና ዳንስ በኋላ ማስተማር ቀጠለ። በዚህ ትምህርቱ አጋጣሚ የሆነ አዋቂ ሰው አግኝቶት የዚህ አለምን የከንቱ ከንቱነት ሰማ። ይህ ጉዳይ በዞራስተር ላይ መወላወልን ፈጠረ። ዞራስተር የሰው በላይን መምጣት ቢሰብክም ይህ እራሱ ከንቱ እንዳልሆን ምንስ ምክንያት አለ? ዞራስትራስ የህይወትን ትርጉም እንዳወቀ ምንስ ማስረጃ አለ፣ የዞርስተር ፍልስፍናስ ካለፉት የስው ልጅ ባህሎችና አስተያየቶች ልዩ እንደሆነ ምንስ ማስረጃ አለ?

በዚህ ውዥንብር ውስጥ ያለው ዞራስተር እንቅልፍ ወስዶት ህልም ተመለከተ፣ በህልሙ ከፍተኛ ነፋስ ተነስቶ የሬሳ ሳጥንን ሲገለብጥ፣ ከሬሳ ሳጥኑ "ህጻናት፣ መላዕክት፣ ጉጉት፣ ጅሎችና ግዙፍ ቢራቢሮወች" እያመለጡ ሲወጡ አየ። በድንጋጤ የነቃው ዞራስተር ስለህልሙ ለአንድ ተከታዩ ነገረው። ተከታዩም ንፋሱ የዞራስተር ትምህርት ምልክት ሲሆን አጠቃላይ ህልሙም የቀድሞውን የሞተ ባህል ማጥፋቱንና በምትኩ አዳዲስ እምቅ

ሃይላትን ማውጣቱን ይሳያል አለው። ዞራስተር ግን ጥርጣሬው ሊበርድ አልቻለም። የወደፊት አለም ነጻ አውጪ ከመሆን ይልቅ የሞተው የኋለኛው ዘመን ባህል አካል እንዳልሆነ እራሱን ሊያሳምን አልቻለም።

ከዚህ በኋላ የነበረበትን ቦታ ለቆ ጉዞ ጀመረ። በጉዞው አንድ አዋቂ ጎባጣ ዞራስተር ለተከታዮቹና በራሱ ጭንቅላት ውስጥ ለራሱ የሚያስተምረው የተለያየና ግብዝ መሆኑን ነገረው። ዞራስተር በዚህ ጊዜ ትልቅ ስህተት በፍልስፍናው ውስጥ እንዳለ ተገነዘበ። ለተከታዮቹም ሆነ ለራሱ የማይነግረው፣ በተጨማሪ ለራሱ እንኳ የማያምነው ትልቅ ችግር እንዳለ ተገነዘብ። ይህ ነገር ምን እንደሆነ በግልጽ ሊረዳ አልቻለም ግን ጭላጭሉ ነበረው።

"ጭር ያለው ሰዓት" ባለው የመጨረሻው ክፍሉ ዞራስተር ድምጽ ከሌለው ድምጽ ጋር ሲከራከር እናነባለን። ድምጹ "የዞራስተር ፍራፍሬወች ቢጎመሩም፣ ዞራስተር ግን ለፍራፍሬወቹ እንዳልጎመራ" አስረዳው። ይህም በዞራስተር ስብዕናና በሚያስተምረው ትምህርት መካከል ልዩነት እንዳለና ዞራስተር ግብዝ እንደሆነ ስለሆነም ስብዕናውን በመቀየረ እራሱን ማሻሻል እንዳለበት ተረዳ።

> ይህን በምሳሌ እነግራችዋለሁ። ትላንትና ፣ ጸጥታ በሰፈነበት ሰዓት፣ ድንገት ከእግሬ በታች ምድር ተንሸራታ ጠፋች፡ ህልሜም ጀመረ። የጊዜ እጅ ወደፊት በሚነጉድበት፣ የህይወቴ ሰዓት ትንፋሹን በዋጠበት የሰማሁት ጸጥታ ልቤን በፍርሃት ሞላው።
> በድንገትም ያለምንም ድምፅ አለኝ "ታውቃለህ ዞራስተር?"
> ሹክሹክታው ስላስፈራኝ ጮኽኩ፣ ፊቴም ገረጣ፣ ግን ካፌ ድምጽም አልወጣም!
> ቀጠለም "ዞራስተር ታውቃለህ ግን አትናገርም!"
> በመጨረሻ በሚገዳደር ቃል ተናገርኩ "አወ! አውቃለሁ ግን መናገር አልፈልግም!"
> ድምጽ የሌለው ሹክሹክታ ግን ጠየቀ " አትፈልግም? ይሄ እውነት ነው? በመገዳደር ቃል እራስክን አትደብቅ!"
> በዚህ ወቅት አለቀስኩ፣ እንደህጻንም ልጅ ተንቀጠቀጥኩ፣ መለስኩም፡ "ስለእውነትስ እፈልግ ነበር! ግን እንዴት አድርጌ? እባክህ ተወኝ! ይሄ ከኔ በላይ ነው!"
> ድምጽ የሌለው ሹክሽክታም መለሰ፣ አለም "አንተ ማን ነህ ዞራስተር? ይልቁን የምትናገረውን ተናገርና ሙት!"

ከዚህ በኋላ ዞራስተር ተከታዮቹን ለሁለተኛ ጊዜ በመተው ወደ ብቸኝነቱ ዋሻ ተመለሰ።

## ክፍል ፫

> "ከትልቁ ተራራየ ፊት ቆምኩ፣ ከሩቁም መዋተቴ እንዲሁ። ለዛም ስል መጀመሪያ ወደ ጥልቁ ገደሌ፣ ወደ የሚያመኝ ስፍራ፣ ወደጥቁሩ ጎርፌ መውርድ አለብኝ"

በማለት ዞራስተር ከተከታዮቹ ተለይቶ ከባዱን ስራውን ለመፈጸም ባዘነ። ግቡም የ"በላይ ሰው"ን ማስተማር አቁሞ እራሱ የበላይ ሰው ለመሆን ነበር።

> "መሰላል ከሌላችሁ በራሳችሁ ጭንቅላት ላይ መወጣጣትን ልመዱ፤ በሌላስ በምን መንገድ ወደላይ ለመውጣት ትሻላችሁ? በጭንቅላታችሁ፣ ከልባችሁ እርቃችሁ... ከዋክብቶቻችሁ ሳይቀሩ ከግራችሁ

> በታች እስኪሆኑ ወደ ላይ ተወጣጡ!"

ዞራስተር በከተሞችና በባህር ጠረፎች በሚዋትትበት ዘመን መንፈሱን ወደታች ስለሚጎትተው የስበት ሃይል ማውጣት ማውረድ ጀመረ። ይህ ሃሳቡን ወደታች የሚጎትተው መንፈስ ባለፈው ክፍል አዋቂው የነገርው የ«ሁሉ ነገር ከንቱነት ነበር። ሁሉም ወደ ላይ የተወረወረ ነገር ወደ መሬት መልሶ ይወድቃል፣ ስለሆነም ሁሉም የከንቱ ከንቱ ነው!»

ዞራስተር ይህን ወደታች የሚጎትት የስበት ሃይል ለማሸነፍ የሁሉ ነገር ዘላለማዊ መመላለስን ሃሳብ ማውጣት ማውረድ ጀመረ። በአለም ላይ ያለው የቁስ ብዛት የተወሰነ ሲሆን ጊዜ ግን የማያልቅ ጅረት ነው። ስለሆነም በቁስ ውስጥ ያሉት እያንዳንዱ አተሞች የሚደረደሩበት መንገድ ስፍር ቁጥር ባይኖርውም... ከጊዜ ወሰን የለሽ የትየለሌንት አንጻር እያንዳንዱ የአቶም አደራደር ዘዴ ተመልሶ ይመጣል። እያንዳንዱ ቁስ ያለፈበትን አደራደር በዘመናት ይደግማል። ሁሉም ነገር ተመልሶ ይመጣል። ሁሉም ኅልው ነገር ካሁን በፊት ኅልው ነበር ስለዚህ መጭው ዘመን እንደ በፊቱ ነው።

> "ኦ! ዞራስተር" አሉ እንስሳቶቹ "ሁሉም ነገር ይሄዳል፣ ሁሉም ነገር ተመልሶ ይመጣል፣ ለዘላለም የህልውና ጎማ ይሽከረከራል። ሁሉም ይሞታል፣ ሁሉም እንደገና ያብባል፣ የህይወት ቀለበት በንዲህ መልኩ ለዘላለም ይቀጥላል። ሁሉም ይሰበራል፣ ሁሉም እንደገና ይጋጠማል፣ ላለም እስከ ዘላለም አንድ አይነት የኅልውና ቤት ይገነባል። ሁሉም ይለያያል፣ ሁሉም ከሁሉ ጋር እንደገና ይገናኛል፣ ለዘለዓለም የኅልውና ቀለበት በራሱ ላይ እንዲህ ይሽከረከራል።"

ጊዜ እንደ መስመር ቀጥ ብሎ የተሰመረ ሳይሆን፣ ላለም እስከ ዘላለም ክብ ሰርቶ በራሱ ላይ የሚሽከረከር እንጂ። "ቀጥ ያለ ሁሉ ውሸት ነው፣ ሁሉም እውነት የተንጋደደ ነው! ጊዜ ራሱ ክብ ነው!"

ነገር ግን የዘላለም መመላስ ዞራስተርን ከማስደሰተ ይልቅ በጣም በጠበጠው። በዚህ ፍልስፍና መሰረት ሁሉ የሰው ልጅ የበላይ-ሰው ለመሆን የሚያደርገው ጥረት መና ሆነ እንደገና ወደ ነበረበት ዝቅተኛ ስብእና ጊዜውን ጠብቆ ይመለሳል። የበላይ ሰው ማለት የሰው ልጅ በትግል የወጣው ተራራና ከዚህም ተራራ ተነስቶ ወደ የበለጠ ከፍታ የሚወጣጣበት ሳይሆን በአዙሪት ውስጥ ያለ አንድ አልባሌ ነጥብ ሆነ። ሃሳቡ ዞራስተራን ክፉኛ አውኮት ሲቆዝም የአንድ ወጣት እረኛ ታሪክ በራዕይ መልኩ ታየው። እረኛው ጉሮሮ ውስጥ ጥቁር እባብ ተሰንቅሮ መተንፈሻ አሳጣው። እባቡንም ከጉሮሮው መንግሎ ለማውጣት የማይቻል ሆነ፡፡ በዚህ ጊዜ ዞራስተር ድምጹን ከፍ አድርጎ "እራሱን ግመጠው!" ብሎ ለዕረኛው ጮኸ። ዕረኛውም የተባለውን በማድረግ የእባቡን እራስ ቱፍ ሲል የነጻነትን ሳቅ ያቀልጠው ጀመር። ከዚህ ጀምሮ ዞራስተር አንድና አንድ አላማ ብቻ ህይወቱን ገዛ፣ እርሱም ወደታች የሚጎትተውን መንፈስ በማሸነፍ ልክ እንደ እረኛው የነጻነቱን ሳቅ መሳቅ።

ዞራስተር ከብዙ ጉዞ በኋላ ከተራራው ዋሻ ደረሰ። በዚህ ክፍል መጨረሻ ዞራስተር ያወከውን ወደታች የሚጎትተውን መንፈስ ሲያሸንፍ እናነባለን። የዘላለም መመላስን ተስፋ አስቆራጭ ሃሳብ ያሸነፈው እንዲህ ነበር፡ ጊዜ ክብ ከሆነ፣ እክቡ የትኛው ላይ ኅልው እንደሆን (የት ላይ እንደምንኖር) ምንም ለውጥ አያመጣም፣ በየትኛው የዕድገት ደረጃ ላይ ኅልው መሆናችንም ምንም ለውጥ አያመጣም፣ "ሁሉም ቅጽበት ላይ ኅልውና ይጀመራል... መካከሉ ሁሉም ቦታ ነው።" ብዙ ሰወች ባለፈው ዘመን ይኖራሉ (ማለት በትውፊት፣ ባህል፣ ካለፉት ዘመናት በተወረሱ የግብረገብ ህግጋት፣ ወዘተ...ስር)። ዞራስተር ደግሞ ወደፊት በሚመጣው፣ ባልተፈጠረው አለም ባህል ይኖር ነበር። ሆኖም ግን ዞራስተር እንደተገነዘበ ያለፈውና መጭው ዘመን ምንም ዋጋ የላቸውም፣ ህይወትን መኖር በአሁኗ ቅጽበት ነው። የህይወት ትግል የሚካሄደው በዚች ቅጽበት ሲሆን ህይወትም የሚገለጸው ኗሪው በትግሉ ውስጥ በሚያሳየው ብርታት ነው። ከዚህ አንጻር የዘላለም ምልልስ ተስፋ የሚያስቆርጥ ጽንሰ ሃሳብ ሳይሆን ከሃይማኖት ውጭ የሆነ አዲስ አይነት የሚያስደስት ዘላለማዊነት ሆነ።

ስለሆነም ዞራስተር ከነበረበት ተውከት ዳነ። ለዚህም ሲል መዝፈንና መደነስ ጀመረ። መዝፈንና መደነስ ከመናገር አንጻር የበለጠ ሃይል አላቸው፡ መናገር ከሰውነታችን የተቆረጠ፣ የንቃተ ኅሊና ስራ ሲሆን መዝፈንና

መደንስ ግን ከሰውነታችን ጋር የተያያዙ እንቅስቃሴወች ስለሆኑ ንቃተ-ኅሊናንና አካላታችንን አንድ ላይ የሚያሳትፉ ስራወች ናቸው። መዝፈንና መደነስ የሚችል ሰው ሙሉ ስለሆነ ህይወቱም ከአዋቂ አስተማሪወች ይልቅ በአሁኗ ቅጽበት የሚካሄድ ነው። ዞራስተር አስተማሪ በነበረበት ጊዜ የተሰማው ጎደሎነት ከዚህ አንጻር ነው። መዝፈንና መደነስ ባለመቻሉ ጎድሎ ነበር።

ለማጠቃለል ያክል፣ የመጽሃፉ የመጀመሪያ ክፍል የ"በላይ ሰውን" መምጣት የሚሰብክ ሲሆን፣ እጅግ በለመለሙና ጣፋጭ በሆኑ እይታወች የታጀበ ነበር። ክፍሉ ከተዘበራረቀው የባህል ፍርክስካሽ የተስተካከለ ስልጣኔን ለመገንባት የሚጥር ነው። ሆኖም ሁሉም የተስተካከለ ነገር የተሸሸገ ዝብርቅርቅ አስከፊ ነገር ስላለው፣ ይህም አስከፊ ነገር ዞሮ ዞሮ እራሱን የበላይ ስለሚያደርግ፣ ይህን መጋፈጥ ግድ ይላል። የአፖሎ ቀን ያለ ዳዮኒስ ጭለማ ሳልው አይሆንም። ማታው እንዳውም ከቀኑ በጣም ሃይለኛ ነው። እኒህ ጭለማ የሆኑ የህይወት ኃይሎች እጅግ ሃይለኛ ስለሆኑ ሰወች ብዙ ጊዜ ከህይወት መራቅ ይመርጣሉ፣ ስለዚህም በብዙወች አስተያየት ህይወት እጅግ ስቃይ የበዛበትና መጥፎ ሲሆን፣ ኑሮ መሸነፍ ያለበት ነገር ነው ብለው ያምናሉ። የዞራስተር አላማ እንግዲህ ምንም እንኳ ህይወት ብዙ ጊዜ ሸብር ቢኖረውም፣ መጥፎውም ቢበዛም ህይወት መኖር ያለበትና መደገፍ ያለበት እንደሆነ ማሳየት ነው። የመጽሃፉ የመጨረሻ ክፍል የዋናወቹ ገጸ ባህርያት ወደ ህይወትን ከነሽብሩና ጭለማው መውደድን ሽግግር ይተርካል። ከብዙ ማሰብና ማስተማር በኋላ - ህይወትን መኖር፣ ህይወትን ማፍቀር። የሚያይ፣ የሚሰማው፣ የሚያውቅ ፍቅር።

ከዘላለም መመላለስ በተጨማሪ ኒሼ ስለ አዳዲስ ህግጋት/ዋጋወች ማውጣት በዚሁ ክፍል አጥብቆ አስተምሯል።

> "በተሰባበሩና ግማሽ ድረስ በተጻፈባቸው ጽላቶች ተከብቤ ተቀምጨ እጠባበቃለሁ። ከቶ መቼ ይሆን የኔስ ጊዜ?"

## ክፍል ፬

የመጀመሪያወቹ ሶስት ክፍሎች ያለምንም ችግር በራሳቸው አንድ የተሟላ ጽሁፍ ይወጣቸዋል፣ ከዚህ አንጻር አራተኛው ክፍል የኒህ የሶስቱ አካል ይሁን እራሱን የቻለ ክፍል ይሁን የሚለው በተመራማሪወች ዘንድ ክርክር አለ። በዚህ ክፍል ዞራስተር አርጅቶ እናገኘዋለን። እንደድሮው ከተራራው ወርዶ ማስተማር አቁሞ የሚፈልጉት ሰወች ተራራው ድርስ መጥተው ትምህርት ሲወስዱ እናነባለን። ዞራስተር ከትልልቅ ሰወች ጋር በመገናኘት እራሱን በኒህ ሰወች ይከባል፣ ምግብንም ከነሱ ጋር ይካፈላል። እነዚህ ታላላቅ ሰወች፡ የግራና የቀኙ ንጉሶች፣ የአረጀው ምትሃተኛ፣ የሮማው ፓፓ፣ ፈቃደኛው ለማኝና ጥላው፣ ንጹህ አዕምሮ፣ በጣም ፉንጋው ሰው ናቸው። ሁሉም በአዕምሮአቸው ትክክል ነው ብለው የተቀበሉት ነገር ትክክል ሳይሆን (አምላክ፣ እውነት፣ ልብ) ተጣሞባቸው ስላገኙ፣ ሆኖም ግን ከዚህ በመነሳት ውሳኔ ላይ መድረስ አቅቷቸው ተስፋ የቆረጡ ነበሩ። በዚህ ምክንያት ድሮ ይሰሩት የነበረውን ስራ መስራት አቅቷቸው የድሮው ስራቸው ተዋናይ/ገጸ ባህርይ ወደ መሆን የወረዱ ነበሩ። ለነዚህ ሰወች ሃዘን ሊገባው የነበረው ዞራስተር ከሃዘኑ ጋር ትንቅንቅ በመፍጠር ሃዘኑን ማሸነፍ እንዳለበት ያሳያል።

> [...] "የመጨረሻው ጥፋቴ ምን ይሆን?" ብሎ እራሱን ጠየቀ
> ከዚህ በኋላ ዞራስተር ወደ ራሱ አዕምሮ አተኮረ፣ ከትልቅ ድንጋይ ላይ ተቀምጦም አንሰላሰለ። በድንገት ተስተካክሎ ተቀመጠ፣ መለሰም፦
> "ለታላላቆቹ ሰወች ከንፈር መምጠጥ! " በዚህ ጊዜ ፊቱ ወደ ንሐስ ተቀየረ

ከዚህ በኋላ በዚህ ክፍል ዞራስተር እንደ አዲስ ሰው ተቀየረ፣

> [...]"አንበሳውም መጥቷል፣ ልጆቸም ተቃርበዋል፣ ዞራስተርም በስሏል፣ ሰዓቴም ተቃርቧል፦ ጎሄ ቀደደ፣ ቀኔ ጀመረ፣ ተነሳ! ተነሳ! አንት ድንቅ ቀትር!"
> እንዲህ በመናገር ከድቅድቅ ተራራ መካከል እየተፈናጠቀች እንደምትወጣ የንጋት ጮራ እያብረቀረቀ ዞራስተር ዋሻውን ለቆ ወጣ።